የሰ/መ/ቁ 254986

ሰኔ 27 ቀን 2016ዓ.ም

ዳኞች፡ ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

እንዳሻው አዳነ

ተሾመ ሽፈራው

ዋዚሞ ዋሲራ

ሡናይት አድነው

አመልካች፡ ዳውንት ወረዳ ግብርና ጽህፈት ቤት

ተጠሪ፦ አቶ አሰሜ ግዴ

መዝገቡ ለሰበር ሰሚ ችሎት ሊቀርብ የቻለው ጉዳዩ በሰበር አጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ በ16/4/2016ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰበር ችሎት እንዲታይ መዝገቡን በመምራቱ ነው፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የኣማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ.03 39217 በቀን 23/2/2016ዓ.ም በዋለው ችሎት የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በማጽናት የሰጠውን ትእዛዝ በመቃወም ነው፡፡

አመልካች ህዳር 7 ቀን 2016 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በተሰጠው ውሳኔ ላይ ተፈፅሟል ያለውን መሰረታዊ የህግ ስህተት ዘርዝሮ በዚህ ችሎት እንዲታረምለት ጠይቋል፡፡ ይህ ችሎትም የቀረበውን አቤቱታ መነሻ በማድረግ መዝገቡን መርምሮ ተከታዩን ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

## ትእዛዝ

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ መንግስት እና ህገ መንግስቱን መሰረት አድርጎ በወጣው የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 መሰረት ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው የዳኝነት ሥልጣን መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸውን ማናቸውንም የመጨረሻ ዉሳኔዎችን መርምሮ ማረም ስለመሆኑ የህገ መንግስቱ አንቀጽ 80 (3) (ሀ) እና የአዋጁ አንቀፅ 10 ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ ተጠሪ በአመልካች ላይ በስር ዳውንት ወረዳ ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ አመልካች በ1997ዓ.ም ከነበረኝ መሬቴ ላይ ምትክ እና ካሳ እሰጥሀለሁ በማለት ቃል ገብቶ መሬቴን ቀንሶ በመውሰድ የማህበረሰብ አቀፍ ኩሬ ያስቆፈረ ቢሆንም ምትክ እና ካሳ ያልሰጠኝ ስለሆነ ምትክ እና የተጣ ገቢ ካሳ ብር 300,000.00 እንዲከፍለኝ ይወሰንልኝ የሚል ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

አመልካች ያነሳውን የይርጋ መከራከሪያ እና መሬቱ የተወሰደው በስምምነት ስለሆነ ክሱ ውድቅ ይደረግልኝ በማለት ያቀረበው መከራከሪያ ውድቅ ተደርጎ አመልካች ለተጠሪ ምትክ ቦታ እና ከሳ ብር 300,000.00 እንዲከፍል ውሳኔ የሰጠ ሲሆን በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የአሁን አመልካች ለሰሜን ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ባቀረበው የይግባኝ ቅሬታ መነሻነት ፍርድ ቤቱ አመልካች መሬት መውሰድም መስጠትም አይችልም ወስዷል ከተባለም ያለአግባብ ቢሆንም መልሶ መስጠት አይችልም በማለት ምትክ ቦታ ይሰጥ የተባለውን ውሳኔ በመሻር የካሳ መጠን ተጣርቶ እንዲወሰን ወደ ስር ፍርድ ቤት የመለሰው በመሆኑ የአሁን ተጠሪ ለክልሉ ጠቅላይ ፍድ ቤት ይግባኝ ቅሬታቸውን በማቅረባቸው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ምትክ ቦታ ሊሰጥ አይችልም በማለት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር ምትክ ቦታ ይሰጥ ካሳው ተጣርቶ ይወሰን ዘንድ ወደ ስር ፍርድ ቤት መመለሱ ተገቢ ነው በማለት ሲወስን የክልሉ ሰበር ችሎትም ይህን ውሳኔ በትእዛዝ ማጽናቱን ከስር ፍርድ ቤቶች የውሳኔ ግልባጮች መረዳት ችለናል፡፡

መሠረታዊ የህግ ስህተት ማለት ምን ማለት እንደሆነ በአዋጁ የትርጉም ክፍል በአንቀጽ 2 (4) ስር በዝርዝር ተመልክቷል፡፡ እነዚህም ምክንያቶች (1) በአዋጁ አንቀጽ 2(4/ሀ) ስር በተመለከተዉ መሰረት ሕገ መንግስታዊ ድንጋጌዎችን በሚቃረን አኳኋን በክልል ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠ የመጨረሻ ዉሳኔ፤(2) በአዋጁ አንቀጽ 2(4/ሸ) ስር እንደተመለከተዉ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ዉሳኔ በሚቃረን አኳኋን በክልል ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠ የመጨረሻ ዉሳኔ፤ (3) በአንቀጽ 2(4/ለ) ላይ እንደተመለከተዉ ሕግን አላግባብ የሚተረጉም ወይም ለጉዳዩ አግባብነት የሌለዉ ድንጋጌ ተጠቅሶ የተሰጠ የመጨረሻ ዉሳኔ ሆኖ ይህ ዉሳኔ የተሰጠበት ጉዳይ ለሕዝብ ጥቅም ሀገራዊ ፋይዳ ያለዉ ጉዳይ በሚል በሕጉ ከተጠቀሱት ሦስቱ ምክንያቶች መካከል ቢያንስ አንዱን የሚያሟላ እና ፍትህን የሚያዛባ ጉልህ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት የመጨረሻ ዉሳኔ ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነዉ፡፡

ከዚህ አንጻር የተያዘውን ጉዳይ ስንመለከት የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡

በመሆኑም በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 28(2) እና ይህንኑ ለማስፈፀም በወጣው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀፅ 7(1) መሰረት የአመልካች አቤቱታ ውድቅ ተደርጓል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ አምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም!